# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፓፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 6 ሰኔ 12 2000 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

# የመለስ አገዛዝ ጭካኔ በሳተላይት ፎቶግራፍ ተጋለጠ

## የግንቦት7 ንቅናቄ የኦጋዴኑን ጭፍጨፋ አጥብቆ አወገዘ

የግንቦት 7 የፍትህ፣የነፃነት እና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፤የአቶ መለስ አገዛዝ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የፈፀመውን የጅምላ ጭፍጨፋ አጥብቆ አወገዘ።የአሜሪካ ሳይንቲስቶች ሰሞኑን ይፋ ያደረጉትን የሳተላይት ፍቶግራፍ መረጃ ተመስርቶ ሂውማን ራይት ዎች እንዳመለከተው፤ ሰላማውያን ዜጎች በሚኖሩባቸው በኦጋዴን መንደሮች ላይ በመለስ አገዛዝ ትዕዛዝ እጅግ ዘግናኝ የጅምላ ጭፍጨፋ መፈጸሙ ተረጋግጧል።

በወገኖቻችን ላይ የተፈፀመውን አሰቃቂ ድርጊት አጥብቆ ያወገዘው የግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነት ና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፤ይህን አረመኔያዊ ተግባር የፈፀሙት የመለስ መንግስት ባለስልጣኖች በአስቸኳይ ህግ ፊት እንዲቀርቡ ዓለማቀፋዊ ጥሪ አስተላልፏል።ሂውማን ራይት ዎች ባለፈው ሳምንት በበኩሉ የሳተላይት መረጃዎችን አስደግፎ ባወጣው መግለጫ ድርጊቱን አጥብቆ ኮንኗል።

የአቶ መለስ አፈ ቀላጤ የሆኑት አቶ በረከት ስምኦን ድርጊቱን ለመካድ ያደረጉት ሙከራ ፈፅሞ ባልጠበቁዋቸው የሳተላይት መረጃዎች መቅረብ አማካይነት ሳይሳካላቸው ቀርቷል።ጭፍጨፋው በሳተላይት ቀረፃ ተደግፎ መቅረቡን የተረዳውና ይህንኑ አስመልክቶ ከሂውማን ራይትስ ዎች ተቃውሞ የቀረበበት የአሜሪካ መንግስት፤ጉዳዩ አሜሪካን ሊያስጠይቅ እንደማይችል፤ይልቁንም ይህ እንዳይፈፀም የኢትዮጵያ መንግስትን ሲመክር እና ሲያሳስብ መክረሙን አስታውቁዋል።"እኛ አስቀድመን ይህ እንዳይፈፀም ነግረናቸው ነበር"ሲሉ አንድ ከፍተኛ የአሜሪካ ባለ ስልጣን ጣታቸውን ወደ መለስና መንግስታቸው ቀስረዋል።

የመግለጫውን ሙሉ ቃል በገጽ 4 ይመልከቱ

**የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ህዝብ ከመጨፍጨፍና የሃገር ሃብት ከመዝረፍ ወንጀሎች ወደ መጨረሻውና ከፍተኛው ወንጀል ተሸጋግሯል።**

**ከእዚህ ቀደም አገዛዙ የፈጸመው የሃገራዊ ክህደት ወንጀል አልበቃ ብሎት፤ ሃገራችን ኢትዮጵያን የመግደል ከፍተኛ ወንጀል እየፈጸመ ነው። ሰፊ የሃገራችንን መሬት ለሱዳን፤ በገንዘብ፤ በነዳጅና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች ሸጧል።**

**ወገኔ፤"አገር የሞተ እለት ወዴት ይደረሳል?" የሚለውን የቀደምቶቻችን ጥያቄ የሚያስነሳ ዘመን ላይ ደርሰናል። ምከር! ተሰባሰብ ! ተደራጅ ! ሳትወድ ተገደህ ለምትገባበት አገር የማዳን የአያት የቅደመ አያት እዳ ቀበቶህን አጥብቅ! መቀነትሽን አጥብቂ!**

### የግንቦት7 ንቅናቄ በተለያዩ የአውሮፓ ሃገራት ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ ላይ ነው። በተለያዩ የአሜሪካን ግዛቶች ተመሳሳይ ስብሰባዎች እንደሚኖሩ ይጠበቃል

የግንቦት 7 የፍትህ፣የነፃነት እና የዲሞክራሲ ንቅናቄ መስራቾች አንዱ የሆኑት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ባለፈው ሳምንት በአውሮፓ የጀመሩትን የስራ ጉብኝት በተሳካ ሁኔታ በማካሄድ ላይ ናቸው።በዶ/ር ብርሃኑ የሚመራ ቡድን ከተለያዩ የአውሮፓ መንግስታትና የፖለቲካ መሪዎች ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት እያካሄደ ነው።

የንቅናቄውን አመሰራረትና አላማ በተመለከተ በብሪታኒያ፣በኔዘርላንድ እና በጀርመን ከሚገኙ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያውያን ጋር ውጤታማ ውይይት ያካሄዱት ዶ/ር ብርሀኑ፤ በያዝነው ሳምንትም በኖርዌይ፣ በስዊድን፣ በቤልጅየም፣ እንደገና በእንግሊዝ እና በሌሎች የአውሮፓ አገሮች ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን እና ከየመንግስታቱ ተወካዮች ጋር ተመሳሳይ ውይይት ለማድረግ ሰኞ ማምሻቸውን ከአምስተርዳም ወደ ኦስሎ አቅንተዋል።

፡ወደ ገጽ 2 ዞሯል፣

### ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ብቃት የሌላቸው መምህራን እየተመደቡ ነው።

በ15000 የአሜሪካን ዶላር ዲግሪያቸውን ሲሸምቱ ከኖሩ፣ የምሁር ጥላቻቸው ገደብ ከሌለው ገዢዎች፣ ትምህርትንና እውቀትን ከሚያረክስ ተግባር ውጭ ምን ይጠበቃል፡፡ እየሆነ ያለው ይህ ነው፡፡ መቼም የመለስ ዜናዊ ጉድ ማለቂያ የለውም፣ ማንም እንደሚገነዘበው በአለፉት 17 የወያኔ የግዛት አመታት በሀገራችን የትምህርት ደረጃ ከዝቅተኛ ትምህርትቤቶች አንስቶ እስክ ከፍተኛ ተቋማት ደረስ ያሳየው የደረጃና የጥራት ማሽቆልቆል አዲስ ሪኮርድ አስመዝግቧል። የአንድ ሀገር እድገት ከትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት ፈጽሞ ትርጉም እንዳይኖረው አድርጎታል።

ትምህርት በሌላ መልኩ የአንድ ሀገር የወደፊት ተረካቢ ዜጋ መቅርጫ ዋና መሳሪያ ነው። በእኛ ሀገር ግን በስልጣን ላይ ያለው ቡድን እራሱን የሀገር መሪ አደረጎ ስላመይቆጥረ የልቁንም ተምህርት የብሄራዊ አድነትን መገንቢያና ማጠናከሪያ መሆኑ ቀርቶ፣ የዘርኝነት ማጠናከሪያ፣ ህዝበን መከፋፊያ መሳሪያ አድርጎታል።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል፣

# ርእሰ አንቀጽ

## የሃገራችንና የህዝባችን ስቃይ ለበለጠ ተግባር ይጠራናል

የመለስ አገዛዝ ባህርይ ላይ የሃሳብ ልዩነት የለንም :: የህዝብ ወገኖች በሙሉ፤ ይህ በህዝብ ይሁንታ መለወጥ ያልፈቀደ ሥርአት፤ በህዝብ ትግል መውደቅ እንዳለበት ይስማማሉ:: በህዝብ ትግል ሲባልም፤ የህዝብ ወገኖች ከምሬታቸውና ዝግጅታቸው ጋር በሚመጥን ማንኛውም መንገድ ቢገጥሙት ተቀባይነት አለው ማለት ነው:: እነዚህ የህዝብ ወገኖች ማድረግ የሌለባቸው ነገር ቢኖር፤ የኔ ትግል ስልት ከአንቺ ይበልጣል የሚል የርስበርስ መጠላለፍ ውስጥ መግባትን ነው:: ሃገሪቱ ሰፊ ፤ ህዝባችን ትልቅ፤ ጠላታችን ዐይን ያወጣ በሆነበት ሁኔታ፤ ታጋዩ ሃይል በትግል ስልት ጉዳይ ላይ እርስ በርሱ ቢተቻች ለትግሉ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ይኖራል ብለን አናምንም :: መጀመሪያ ሁላችንም በየተያያዝነው ስልት የጋራ ጠላታችንን እንግጠምና ፤ ኋላ ከድል በሁዋላ ፤ የማ የትግል ስልት የተሻለውን አስተዋፅኦ አደረገ የሚለው ግምገማና ሽልማት ላይ እንሽነጋገላለን ባይ ነን:: መጀመሪያ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚወስደንን ጥርጊያ እንደየአቅማችን፤ እንደየርዕያችን፤ እንደየናፍቆታችን፤ጊዜ ላብና ደማችንን ለትግሉ እናውል እንላለን ::

አዎን በትግል ድርጅቶች መሃል ይህን የመሠለ አርቆ አሳቢነትና የመቻቻል ባህል ሲጠነክር፤ ለጠላት መግቢያ ቀዳዳ ይጠፋል :: ሁሉም እንደአቅሙ፤ እንደምሬቱ፤ እንደስሌቱ በትግሉ ይሰማራ ስንል፤ ድርጅቶቹን ብቻ ማለታችን አይደለም:: ኢትዮጵያውያን ዜጎችንም ጭምር ነው:: ሥርአቱን በተለያየ መንገድ ማዳከም ይችላሉ:: እንኩዋንስ ህዝቡ፤ በመለስ እብሪት የተ በሳጩ የመንግስት ባለስልጣናት ሳይቀሩ፤ የሚያውቁትን መንግስታዊ ምስጢር ለዜና አውታሮች በምስጢር በማጋለጥ የስርአቱን ውድቀት ማፋጠን ይችላሉ:: አንድ በቅርቡ ከደረሰን ምስጢር ብናከፍላችሁ ይህን ይመስላል :: የመለስ አገዛዝ «ለምን በግንቦት 97 ምርጫ በከተሞች በዝ ረራ ተሸነፍን?» የሚል ጥያቄ ለራሱ አንስቶ የሰጠው ምላሽ «የኢትዮጵያ ከተሞች አመሠራረት ከነፍጠኛ ሰፈራ ጋር የተያያዘ ስለሆነ በዋና መልኩ ከተሞች የተያዙት በአማሮች ስለሆነ ነው :: ከሚቀጥለው ምርጫ በፊት ይህን የከተሞች የብሄር ተዋፅኦ ለመለወጥ፤ አምስት ሚሊዮን ኦሮሞዎችን ባብዛኛው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑትን በከተሞች እንዲሰፍሩ የሚያበረታታ ፖሊሲ መጠቀም አለብን» የሚል የፖሊሲ ሃሳብ ይገኝበታል:: በመጀመርያ ይህን የፖሊሲ ረቂቅ ለላከልን ባለስልጣን የተሰማንን አድናቆት በህዝብ ፊት መግለፅ እንወዳለን :: ሌሎችም አርአያነቱን እንዲከተሉ እናበ ረታታለን:: በተናጠል ትንሽ የምትመስል መረጃና ሰነድ ፤ ከየአቅጣጫው ከመጡት ጋር ተገጣጥመው የሚፈጥሩት ስእል ትልቅ ስለሚሆን፤ ዜጎች የትኛውንም መረጃ ኢምንት ነው ብለው ከመላክ እንዳይቆጠቡም እንጠይቃለን:: አድራሻችንም በኢሜይል pr@ginbot7.org ፣የፖስታ አድራሻችንን በዚህ ገጽ መጨረሻ ተመልከቱ ነው ::

ባለሥልጣናት እንኩዋን እንዲህ አይነት ትብብር ማድረግ በጀመሩበት ሰአት፤ ታጋይ ድርጅቶቹ ቀዳሚውንና ተከታዩን መለየት አቅቷቸው፤ እርስ በርስ ሲደናቆሩ፤ የመለስ አገዛዝ ከተወጠረበት ሁኔታ አምልጦ እንዳይጠናከር አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል:: ጊዜው የሚጠይቀው መሰባሰብንም ከልባቸው አምርረው ሊንቀሳቀሱበት ያስፈልጋል እንላለን:: የሁሉም መሰባሰብም ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ፤ ለጊዜው የወቅቱን አጣዳፊነት የተ ገነዘቡት የትብብር ሥራቸውን ማቀላጠፍ ይኖርባቸዋል እንላለን :: ህዝባችን በስቃይ፤ ገዢዎቻችን በተራ እብሪት፤ ሃገራችን በመለሳዊ ክህደት እባጭ ተ ጎንብሳና ተዳክማ የምትገኝበት ሰአት ላይ ነን:: ስቃዩ፣ እብሪቱ ክህደቱ፣ የሚሰማን በከንቱ የምናባክነው ጊዜ ሊኖረን አይችልም :: ከመቆጨታችን ጋር የማይመጥን ባዶ ወሬ ላይ ብቻ የምንጠመድበት ህሊና ሊኖረንም አይገባም:: ጊዜያችንን፤ ኪሳችንን፤ አእምሮአችንን በሚያንገበግበን የህዝባችንና የሃገራችን ብሶት ላይ እንድናውለው «የግንቦት7 ንቅናቄ» ጥሪ ውን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ያቀርባል ::

**በተለያዩ የአውሮፓ ሃገራት** ከገጽ 1 የዞረ

በጀርመን ሃገር ኑረምበርግ ከተማ ዶ/ር ብርሀኑ እና ሌላ የንቅናቄው አመራር አቶ መስፍን አማን፤ ንቅናቄው በአጭር ጊዜያት ውስጥ ያከናወናቸውን ተግባራት ለኢትዮጵያውያኑ በስፋት ከማብራራታቸውም በላይ፡ከተሰብሳቢዎች ለተነሱ ጥያቄዎች ግልፅና ቀጥተኛ ምላሽ ሰጥተዋል።በውይይቱ ከፍተኛ እርካታ እንደተሰማቸው የገለፁት ኢትዮጵያኑ፤ ግንቦት 7 ንቅናቄ ይዟቸው የተነሳቸውን ዲሞክራሲያዊ አላማዎች ለማሳካት ፤ከንቅናቄው ጎን ቆመው የሚችሉትን ሁሉ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል። የንቅናቄው አባል ለመሆን በየዕለቱ ከተገመተው በላይ ጥያቄዎች እየጎረፉ መሆናቸውን የተረዱት ኢትዮጵያውያኑ፤ካለፉት ተሞክሮዎች በመነሳት አባላትን የመቀበል አሰራር ላይ ከፍ ያለ ጥንቃቄ እንዲደረግም ምክራቸውን አስተላልፈዋል። በአባላት አቀባበል ዙሪያ ጠንካራ የአሰራር መዋቅር በመዘርጋቱ ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ በንቅናቄው አመራሮች ተገልጹዋል።

ዶ/ር ብርሀኑ በዚሁ የስራ ጉብኝታቸው ከተለያዩ የአውሮፓ መንግስታት ተወካዮችና የፖለቲካ መሪዎች ጋር ውጤታማ ውይይት እያደረጉ እንደሆነ ታውቋል።በተያያዘም በሚቀጥለው ሳቀምንት ዶ/ር ብርሃኑ ተቀማጭነታቸው ቤልጅየም ብራስልስ ለሆኑ ያውሮፓ ህብረት የፓርላማና የኮሚሽኑ ባላስልጣናት ገለጻ እንደሚያደርጉ ከግንቦት ሰባት የውጭ ግንኙነት ክፍል ከደረሰን መረጃ ለመረዳት ችለናል።በአውሮፓ ህብረት ዋና መስሪያቤት በሚደረገው በዚህ ስብሰባ በወቅታዊ የሃገራችን ሁኔታ፣የሰብአዊ መብት አያያዝ እና የአውሮፓ መንግስታት መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃ ውይይት እንደሚያደርጉ ታውቋል።በእለቱም የኮሚሽኑ የልማት ተጠሪ ሉዊ ሚሼል በቅርብ በኢትዮጵያ ስላካሄዱት ጉብኝትና፣ለመለስ መንግስት ተሰጠ ስለተባለው የገንዘብ እርዳታ ማብራሪያ እንደሚጠየቅ ለማወቅ ችለናል።

**ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት** ከገጽ 1 የዞረ

ቀድም ሲል በወጣው የትምህርት ሥርአት ለውጥ ከአስረኛ ክፍል ድርስ ትምህረት የጨረሱ፣ የአስራ ሦስትና የአስራ አራት ዓመት ልጆችን፣ በሙያ አስልጥኖ ለስራ ማብቃት የማስቻሉን ሙከራ፣ በእኔ ክልል አይፈጸምም በማለት የትግራይ ክልል እራሱን ሲያገል፣ በሌሎች ክልልሎች ሙከራው እንዲደረግ ተደረገ። ከብዙ አመታት ከፋተኛ ወጭና በጊዜው የተገኙትን ተማሪዎቹ የወደፊት እድል ከገደለ በኋላ እንደገና ወደ ዱሮው ለመለስ ተወስኖል። ከዚህም በተጨማሪ በትግራይ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚያስተምሩ አስተማሪዎችና ሰራተኞች ከሁለት አመት የስራ ዘመን በኋላ ወደ ውጭ የመሄድና የቀጣይ ትምህርት እድል ስለሚያስገኝ፣ ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ወደ ትግራይ ለመሳብ ችለዋል። በዜና ዘጋቢያችን መሰረት፣ ይህ ሁኔታና በተለያዩ ምክንያት ወደውጭ ወጥተው የማይመለሱት የከፍተኛ ትንምህርት አስተማሪዎች፣ ያለ እቅድ በየቦታው የሚከፈቱት የትምህርት ተቋማት ተጨምሮበት፣ ከትግራይ ክልል ውጭ ያሉት የትምህርት ተቋማት ያጋጠማቸውን ከፍተኛ የአስተማሪ እጥረት ወደ ገጽ 4 ዞሯል

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ የቀድሞ
የአዲስ ዜና እና የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፤ አቶ መስፍን አማን፤አቶ ቾኮል ጌታሁን፤ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ።

# አገር ይፈርሳል፣ እኛ ተኝተናል

ከሳምሶን በእርሱፈቃድ(ለውይይት የቀረበ)

ኢትዮጵያ አዲሲቷ ሶማሊያ የመሆኛዋ ጊዜ በፍጥነት እየቀረበ የመጣ ይመስለኛል።ከጠራ ሰማይ ላይ ተነስቼ አይደለም ከዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰኩት።ዛሬ አገሪቱ የገጠማትን ፈተናና ፈተናውን ለማለፍ ገዚዎች የተባሉት እየወሰዱ ያለውን እርምጃ ስንመለከት፣ብዙዎቻችን ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ ልንደርስ እንደምንችል አስባለሁ።ሶማሊያ ለምን ፈረሰች?ሶማሊያ ለመፍረሷ ብዙ ምክንያቶችን መደርደር ይቻል ይሆናል።ምክንያቶቹን ወደ መዘርዘሩ ባልገባም፣ሶማሊያ ከመፍረሷ ጥቂት አመታት በፊት ልክ አሁን ኢትዮጵያ የምትገኝበት እይነት ሁኔታ ውስጥ ትገኝ እንደነበር መረጃዎችን ዋቢ አድርጎ መናገር ይቻላል።በ1980ዎቹ፣አምባገነኑ የሲያድባሬ አገዛዝ ለተሻለ አስተዳደር የተነሱትን የሶማሊላንድና የሌሎች አካባቢ ህዝቦችን መጨፍጨፉ ሳያንስ፣ አገሪቱ በርሀብ፣በድህነትና በውጭ የፖለቲካ ሀይሎች መዳፍ ስር ወድቃ ነበር።ምንም እንኳን ኢትዮጵያም በጊዜው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበረች ቢሆንም፣ለህዝቦቿ ምስጋና ይግባና፣ ከመፈረካከስ ለመዳን ችላለች።ዛሬ ደግሞ ከ17 አመታት የመለስ ዜናዊ የተበላሸ አገዛዝ በሁዋላ፣ የአገሪቱ ህልውና በ1980ዎቹ መጨረሻዎች ወደነበረበት አጣብቂኝ ተመልሶ ገብቷል።ዋና ዋና ፈተናዎችን እንመልከት።

## ፈተና አንድ፣ የመብት ጥያቄዎች

በአሁኑ ጊዜ ከመብት ጋር በተያያዙ የሚነሱ ጥያቄዎች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየበዙና እየተጠናከሩ መጥተዋል።ግንቦት 7/1997 የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ የተነሳው የመብት ጥያቄ፣የመለስ አገዛዝ ፈጽሞ ሊያጣፋው አልቻለም።ረመጡ ዛሬም ድረስ ተዳፍኖ ይገኛል።የኦጋዴን ህዝብ የተሻለ አስተዳደር ለመመስረት ይዞት የተነሳውን አላማ አጠንክሮ ቀጥሎበታል።የመለስ ወታደሮች የኦጋዴን ሴቶችን ቢደፍሩ፣እናቶችንና ህጻናትን ግንድ ላይ አስረው ቢገርፉ፣ቤታቸውን ቢያቃጥሉ፣ወጣቶችን እያነቁ ቢገድሉ የተነሳውን ቋያ ማጥፋት አልቻሉም።እያደረሱት ያለውን ግፍ ለመደበቅ ቢሞክሩም፣ እድሜ ለሂውማን ራይትስ ዋችና ለአሜሪካን ሳይንቲስቶች፣ ከህዝብ አይን መደበቅ አልቻሉም።እነ መለስንና ግብረአበሮቻቸውን ንጹሀን ዜጎችን በመፍጀት(crime against humanity) እና የጦር ወንጀል በመፈጸም ለመክሰስ ይህ ሰነድ በእጅጉ ይጠቅማል።የኦሮሞ ህዝብም በመለስ ጨቁዋኝ አገዛዝ አልገዛም ብሎ ትግሉን ካፋፋመ ቆየት ብሏል። ኦሮሞ ሁኖ መወለድን እንደወንጀል የሚቆጥረው የመለስ ቡድን፣ስፍር ቁጥር የሌለውን የኦሮሞ ተወላጅ፣ በእስርቤቶች ውስጥ አጉሮ ይገኛል።የመለስ ጥፋት በኦጋዴንና በኦሮሚያ ብቻ የተወሰነ አይደለም።በአማራ፣በደቡብ፣በጋምቤላና በሌሎች ህዝቦች ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ ለመግለጽ የሚከብድ ነው።

ለመብት የሚደረጉት ትግሎች፣ፍትሀዊ የመሆናቸውን ያክል፣ከአገር ህልውና ጋር በተያያዘ የሚፈጥሩዋቸው ችግሮችም አሉ።አብዛኞቹ ለመብት የሚታገሉ ድርጅቶች ተለያይቶ መኖርን፣እንደመፍትሄ የሚወስዱ ናቸው።ወያኔ በ17 አመት እድሜው ሲሰራ የነበረው እንዲህ አይነቱ ሁኔታ እንዲፈጠር መሆኑ ተብሎ ያለቀለት ነገር ነው።የፖለቲካ ግንዛቤው አናሳ በሆነ ህዝብ ውስጥ የዘር ፖለቲካን በመዝራት ግጭት መፍጠርና ህዝብ እንዲተላለቅ ማድረግ እጅግ ቀላል ነው።አሁን በኢትዮጵያ የተደቀነው ችግርም ይህ ነው።ታዋቂው ምሁር እዝቅያስ አሰፋ ፣ የፖለቲካ መሪዎች የራሳቸውን ድብቅ የስልጣን ጥማት ለማርካት፣ህዝቡን የዘር አጀንዳ በመስበክ እንዲተላለቅ እንደሚያደርጉ በመረጃ አስደግፈው ጽፈዋል።።በኢትዮጵያም ያለው ከመብት ጋር የተያያዘ ችግር፣ የአገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥለውም ይህ ከዘር ጋር የተያያዘው ጨው ስለሚጨመርበት ነው።

## ፈተና ሁለት የዳቦ ጥያቄ

ከመብት ጥያቄ ባለፈ፣በአሁኑ ጊዜ፣ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሲጨነቅ የሚያድረው ነገን ምን በልቼ እኖራለሁ በሚል ነው።በእድሜያችን የጤፍ ዋጋ 1000 ብር ገብቶ ሰምተንም አይተንም አናውቅም።አማካኝ ወርሀዊ ደሞዙ ከ200 ብር የማይዘል ገቢ ያለው ዜጋ፣በእያንዳንዱ ቀን ምንና እንዴት በልቶ እንደሚያድር ስናስብ ኢኮኖሚክሱ ሁሉ እንቆቅልሽ ይሆንብናል።ሰሞኑን ደግሞ አንድ ዳቦ እንኩዋን መብላት ያልቻለው ህዝብ ቁጥር በሚሊዮኖች ጨምራል።ይህ ህዝብ ከውጭ አገራት ምጽዋት እንዳያገኝ እንኳ ግፈኛው የመለስ መንግስት ቁጥሩን እየደበቀና ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር እየተጣላ ይገኛል።የመለስ መንግስት የተራበው 4 ሚሊዎን እንጅ፣6 ሚሊዮን አይደለም እያለ በቁጥር ይጣላል።የምእራባዊ መንግስታት አንድ ሰው ሲራብ እንቅልፍ አጥተው ያድራሉ፣አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ ግን ስልጣኑን አደጋ ውስጥ እስካልጣለው ድረስ ህዝቦች እርዳታ ሳያገኙ ቢሞቱ ግድ የለውም።

አሁን የምናየው ረሀብና የኑሮ ውድነት በተአምር ከልተገታ፣በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የህዝብ ፍልሰት መፍጠሩ አይቀርም።ችግሩ ስደት መሰደዱ ሳይሆን፣ተሰዳጅ የሚሰደድበት ስፍራ መጥፋቱ ነው።የቀድሞዎቹ የሰፈራ ቦታዎች እንደ ጎጃም፣ጋምቤላና ወለጋ ያሉ ቦታዎች እንኩዋንስ ስደተኛ ሊቀበሉ ይቅርና እራሳቸው በችግር እየተቆሉ ነው።በተሰዳጁና ስደትን በሚቀበለው ህዝብ መካከል ግጭት መፈጠሩና የአገሪቱ ህልውና አደጋ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው።የምንሰጋውም ይህንን ነው።

## ፈተና ሶስት፣የድንበርና የደህንነት ጥያቄ

ሀንስ ሞርጋንታው የተባለ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር፣የማንኛውም መንግስት ትንሹ ሀላፊነት ብሄራዊ ደህንነቱን ማስጠበቅ ነው ይላል።የመለስ ቡድን መንግስታዊ ሀላፊነቱን ረስቶ፣መሬት ብለው ለጠየቁት አገሮች ሁሉ ሳያመነታ እንደዳቦ እየቆረሰ ይሰጣል።ሱዳን አባቶቻችን ለዘመናት ተዋድቀው ያቆዩትን መሬት ያለምንም ችግር በቀላሉ ወስዳለች።በራሱዋ የውስጥ ችግር የተተበተበችው ሱዳን፣የመለስን መንግስት አስፈራርታ መሬት ማግኘቱዋ ፣የመለስ አገዛዝ ከሱዳን ባነሰ የሀይል ሚዛን ላይ እንደሚገኝ የሚያሳይ ነው።ዛሬ ሱዳን መሬት ወስዳለች፣ነገ ደግሞ ኬንያና ጅቡቲ ቁናቸውን ይዘው መሬት ስፈሩልን ብለው ወዲ ዜናዊን መጠየቃቸው አይቀርም።ኤርትራና ሶማሊያም መለስን በፍቅር ቢቀርቡት ወይም እንደማይወጉት ማረጋገጫ ቢሰጡት ኖሮ፣መሬት ያለምንም ችግር ማግኘት ይችሉ ነበር።

ኢትዮጵያ "የአገር ጥፋት ልክፍት" ባለው መሪ በመተዳደሩዋ ህልውናዋ እየጠፋ መሆኑ ሳያንስ፣የአካባቢው ሀይሎች ሰይፋቸውን እየሳሉ እና እየጎለበቱ መምጣታቸው ሌላው የስጋት ምንጭ እየሆነ ነው።ከኤርትራ ጋር ያለው ፍጥጫ እንዴት እንደሚቋጭ መላ በጠፋበት ሁኔታ፣በሱማሊያ የእስልምና ሀይሎች እየተጠናከሩ መምጣት፣ከኢትዮጵያ ህልውና ጋር ተያይዞ ችግሮች መፈጠራቸው አይቀርም።ሶማሊዎች የመለስን ወታደሮች ከአገራቸው አባርረው አርፈው ይተኛሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

ከላይ በግርድፉ ያነሳሁዋቸው ፈተናዎች እና እየተሰጡ ያሉት መልሶች፣የኢትዮጵያን ህልውና እየተፈታተኑ መምጣታቸውን በመጠኑም ቢሆን የሚያሳዩ ይመስለኛል።ችግሮቹን ሰፋ አድርገን ብናያቸው፣የአደጋውን መጠን አጉልተው እንደሚያሳዩ አምናለሁ።ሚሰጡ አምናለሁ፣እጋብዛለሁም።

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ቀን ሰኔ 7 2000

# የመለስ አምባገነን አገዛዝ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የሚያደርሰውን አሰቃቂ ግፍና እልቂት የግንቦት7 ንቅናቄ እጥብቆ ያወግዛል፡፡

በማያሻማ ቋንቋና በማያሻማ ማስረጃ ደግፎ፣ የታወቀው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት፣ ህዩማን ራይት ወች፣ የመለስ አገዛዝ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የፈጸመውን የግፍ ወንጀል ከትናንብት በስተያ ሰኔ 4 2000 ዓ.ም ባወጣው ዘገባ አጋልጦታል፡፡

በርካታ መንደሮች በቃጠሎ እንዳልነበሩ ተደርገው ወድመዋል፡፡ ህጻናት፣ ኣዛውንቶች ሴቶች፣ ወንዶች አቅመ ደካሞች በሙሉ በመለስ ዜናዊ ጦር አሰቃቂ የጅምላ ጭፍጨፋ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ሴቶችን እያስገደዱ አስነዋሪ በሆነ መንገድ መድፈር፣ ዘረፋ፣ ማፈናቀልና ማሳደድ ከጭፍጨፋው ጋር በተጓዳኝ እየተፈጸመ ያለ ግፍ ነው፡፡ ይህ ወንጀል መለስ ዜናዊና የግፍ ተባባሪ ጓደኞቹን በከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰትና በሰብአዊነት ላይ በተፈፀመ ከፍተኛ ወንጀል የሚያስጠይቃቸው እንደሆነ የሰብአዊ መብት ተሟገቹ ቡድን በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

ይህ አይነቱ አሰቃቂ ወንጀል በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ መፈጸም ከጀመረ አመታት አልፏል፡፡ አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና በስብአዊነት ላይ የተደረጉ ከፍተኛ ወንጀሎች ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ የጅምላ ጭፍጨፋዎችና የዘር ማጥፋት እርምጃዎች በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በአፋር፣ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞችና ክልሎች የመለስ አገዛዝ ሲፈጽም እንደነበርና አሁንም እየፈጸመ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ይህ በሁሉም የሃገራችን ክልሎች በሁሉም ህዝብ ላይ የመለስ አገዛዝ የሚያወርደው የመከራ ዝናብ ሁላችንንም በጋራ የሚያቃጥል ሆኖ ሳለ፣ እስካሁን እንደታየው ሁላችንም በጋራ በእዚህ መከራ አምራች በሆነ አገዛዝ ላይ በጋራ ተባብረን እንዳንነሳ ሆነናል፡፡ የዚህ ዋንኛው ምክንያት ወያኔ ለከፋፍለህ ግዛ እንዲያመቸው በመሃከላችን የሚያሰራጨው ዘረኛ አመለካከትና የዘረጋው መተባበርና መተሳሰብን ባይተዋር ያደረገ ዘረኛ የፖለቲካ ስርአት ነው፡፡

ሁሉችንም የሃገሪቱ ዜጎች የምንገኝበትን ፈታኝና አሰቃቂ ሁኔታ ማሸነፍ የምንችለው መለስ ዜናዊ ያደራጀውን ግፍ ፈጻሚ ሰራዊትና የስለላ ሃይል፣ የሚያሰራጨውን የከፋፍሎ መግዣ መርዘኛ አመለካከት፣ የአንዱን ዜጋ ጥቃት የሁሉም ዜጋ ጥቃት፣ የአንዱን ክልል ህዝብ ጥቃት፣ የሌላው ክልል ህዝብ ጥቃት፣ አድርጎ በሚያይ የጋራ ተቆርቋሪነት እርስ በእርሳችን ስንቆላለፍ ብቻ ነው፡፡

ይህ የመቆላለፍ እርምጃ ዛሬ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን የሚሰቀጥጥ እርምጃ በአንድ ድምጽ በማውገዝ ይጀመራል፡፡ የኦጋዴን ወገኖቻችን ራሳቸውን እንዲህ አይነቱን ግፍ ለመከላከል በሚያደርጉት ትግል ከጎናቸው መቆማችንን በተግባር ስናረጋግጥ የጋራ ተቆርቋሪነታችን እውን ይሆናል፡፡

ግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በቅድሚያ በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል ይኮንናል፡፡ የኦጋዴን ወገኖቻችን የመለስ ዜናዊን አስከፊና አጸያፊ ጭፍጨፋ ለመመከት የሚያደርጉትን ትግል አቅሙ በፈቀደው በማናቸውም መንገድ ለመርዳት ዝግጁ መሆኑን ያስታውቃል፡፡

በሌላ በኩልም፣ በሃገራችን ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰባትና ሌሎችም ተቋማትና ግለሰቦች በሁሉም የሃገራችን ዜጎች ላይ የሚፈጸምን በደል በደላቸው አድርገው ማየት፣ ይህንን እንዲቆም መንቀሳቀስ የኢትዮጵያዊነት የዜግነት ግዴታ እንደሆነ ተረድተው በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ እንዲያወግዙ፣ ይህ ግፍ እንዲቆም የሚችሉትን እንዲያደርጉ ግንቦት7 ጥሪ ያቀርባል፡፡

ወደፊትም ቢሆን በየትኛውም የሃገሪቱ ክልል፣ በየትኛውም የሃገሪቱ ዜጋ ላይ የሚፈጸምን ግፍና ወንጀል ሁላችንም የሃገሪቱ ዜጎች በራሳችን ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል ልንኮንነውና ልንቃወመው የሚያስችል ዝግጁነት ሊኖረን ይገባል፡፡ በእንዲህ አይነቱ የመተሳሰብና የመቆርቆር የጋራ ስሜት ብቻ ነው፣ መለስ ዜናዊ ሁላችንም ከፋፍሎ እየረገጠ ለመግዛት፣ ካልሆነለት የሃገራችንን አንድነት በማናጋት ህልውናዋን ለማፍረስ ያውጠነጠነውን አደገኛ ሴራ ማምከን የምንችለው፡፡

የአለም አቀፍ ህብረተሰቡም ለአጭር ግዜ፣ ለጠባብ ጥቅምና ፍላጎት ማስፈጸሚያ ሲል እሹሩሩ የሚለውን የመለስን አገዛዝ በቃህ ሊለው ይገባል፡፡ በአፍሪካችን ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ግፈኛ መንግስት በማሞካሸትና አቅም በማጠናከር የሚቀጥሉ የውጭ መንግስታት ድርጊት መቆም አለበት፡፡ ውሎ አድሮ እነዚህ ከመለስ ግፈኛ አገዛዝ ጋር ሽርክና የገቡ መንግስታት ይህን ሽርክናቸውን በፍጥነት ካላቋረጡ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ እነሱንም ቢሆን ከወንጀለኛው የመለስ አገዛዝ ለይቶ ማየት ከማይችልበት ደረጃ ላይ እንደሚያደርሱት ሊያውቁት ይገባል፡፡ ይህም የአመለካከት ክረት ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለእነዚህ የውጭ መንግስታት ዘላቂ ጥቅም የማይበጅ በመሆኑ በተለይ የምእራብ መንግስታት እስካሁን በኢትዮጵያ ላይ ሲያራምዱት የነበረውን ፖሊሲያቸውን በአስቸኳይ ከልሰው የኢትዮጵያ ህዝብ ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል እንዲደግፉ ግንቦት7 ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ግንቦት7 ንቅናቄ
የፖለቲካ አመራር

---

## ከገጽ2 የዞረ የዩኒቨርሰቲ

ለማቃለል በሚል ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የማታ ፕሮግራም ተማሪዎች የመመረቂያ ነጥባቸው ከ2.5 እና በላይ የሆኑትን በአስተማሪነት ለመቅጠርና ለማሰራት ተወስኖ በተግባር ለማዋል እየተሞከረ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የማታው የትምህርት ፕሮግራም ስለሚገኝበት ዝቅተኛ ደረጃን በሚልመለከት በተለያዩ በግል ጋዜጦች ላይ ከፍተኛ ወቀሳ በተደጋጋሚ ሲደርስበት እንደነበረ ይታወሳል።
የዜና ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ ለዚሁ አስተማሪነት የታጩ ተማሪዎች፣ እንዴው ለስሙ የከፍተኛ ተቋም አስተማሪ ነው ከመባልና እንዲሁም በአንዳንድ ተቋማት ከሚገኘው አንስተኛ ጥቅሞች ባሻገር ሌላ ነገር እንደማያስባቸው ለመረዳት ችሏል።በመጨረሻም የዜና ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው በርካታ ሰዎች በሰጡት አስተያዬት መሰረት ዛሬ በእነዚህ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ የሚፈጸመው ወንጀል፣ በተለያዩ አቅጣጫዎች በዘረኛና መሰሪ አመለካከት ወያኔ የኔ ነው የሚለውን የትግራይ ክልል በተቀሩት ክልሎች ኪሳራ ለማስከበር በማስመሰል የሚደረግው ነውረኛ አካሄድ አካል አድርገው እንደሚያዩትና ይህ ሁኔታ ወደፊት የሚፈጥረው ከፍተኛ አደጋ በጣም የሚያሳስባቸው መሆኑን ነው።ለከፋፋይ ዘረኛ ፖሊሲው መፈጸም የተመቻቸ ሁኔታ እየፈጠረ እንዳለ ያሳያል ብለዋል።